# ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በዴንቨር ከተማ ተካሄደ

January 14, 2007 በዴንቨር የኢሕአፓ ተጠሪ ኮሚቴና በፈለገ ብረሀን የኢትዮጵያውያን ሲቪክ ማህበር በኮሎራዶ የጋራ አስተባባሪነት በዴንቨር ከተማ በተካሄደው ስብሰባ ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊ አሜሪካውያን በወቅቱ አስቸጋሪ የነበረው ቅዝቃዜና በረዶ ሳይበግራቸው ግዜ በማይሽረው ፅኑ በሆነው የሀገር ፍቅር ስሜታቸው ብርታት በሚያስደስት ሁኔታ ከቀኑ 3:00pm ላይ ጀምሮ ከምሽቱ 8:00pm ላይ በተጠናቀቀው ስለወቅቱ የሀገራችን ጉዳይን በተመለከተ ሰፊና ትምህርታዊ ሁሉን አቀፍ በሳል የውይይት መድረክ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል።

በወቅቱ የክብር እንግዳ የነበሩት ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል ስለ ኢሕአፓ የረጅም ጉዞ ትግልና ስለኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታዎች፤ የውጭ ሀይሎች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት ምክንያት ለእነሱ ታዛዥና አገልጋይ ለሆነው ለወያኔ ምንግስት ያላቸው ድጋፍ የመስጠት ዝንባሌ የሀገራችንን ሉአላዊነትና የሕዝባችንን መሰረታዊና ዘላቂ ጥቅሞችን ለማስከበር በሀገር ወዳድ ሀይሎች በሚደረገው ህዝባዊ ትግል ላይ እንቅፋት በመሆን በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ረዘም ላለ ግዜ የፓለቲካ አለመረጋጋት በመፈጠሩ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ጦርነት ረሀብና እርዛት በሽታና ሰቆቃ የዕለት ተዕለት ዕጣ ፋንታው እደሆነ ጠቅለል ባለ መልኩ እውነታነት ያለው በመረጃ የተደገፈ ከልብ የመነጨ ሰፊና ትምህርት ሰጭ መግለጫ አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው አሁን ካለንበት ችግር እንዴት እንደምንላቀቅና፤ እንዴት ፀረ-ወያኔ የትግል ስልት እንደምንቀይስ፤ እንዴት ሠላም ድሞክራሲንና የሕግ የበላይነትን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈን በረጅሙ የትግል ልምዳቸው ያካበቱትን በሳል የመፍትሔ ሀሣቦችን ለውይይት በማቅረብ ወቅቱ ከምንግዜውም በላይ የሁላችንንም የጋራ ጥረት አስፈላጊነት በሚጠቁም መልኩ ከአለፈው ታሪካችንና የትግል ጉዞአችን በመነሳት በእውነት ላይ የተመረኮዘ ጥናታዊ ግምገማ በማድረግ ረጅሙ የድሞክራሲ የትግል ጉዞ በአንድነታችን ዋስትና ላይ የመመስረት አስፈላጊነትን በማመን የግልና የቡድንን የፖለቲካ ስሜት ለማስፈፀም የሚደረገውን ሩክክር አቁመን የአንድነት ዕትብታችን ጠንቅ የሆኑትን የጎሣ ፖለቲካን ምቀኝነትን ከኢትዮጵያውያን ባህልና ጨዋነት ያፈነገጡ ባህሪያቶችን ከመጠን ያለፈ እራስ ወዳድነትንና የስልጣን ሱስን አስወግደን እያንዳንዳችን ነፍስ ፈታሽ የሆነ የእራስ ዕውነታን በማዳበር በፍቅርና በዕምነት ላይ የተመሰረተ የአንድነት ሀይላችንን ከምንግዞውም በላይ በማጎልበት አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ በሚል ቅዱስ ራዕይ ስር ተሠባስበን ለውጤት ሊያበቃን የሚችል በሣል የትግል ስልት በመቀየስ ሁለገብ የሆነ የጋራ ትግል ማድረግ ይጠበቅብናል በሚል ዙሪያ ከተሰብሣቢው ጋር ሠፊና ትምህርት አዘል የጋራ መግባባትን ሊፈጥር በሚችል መልኩ ገንቢ ውይይት አድርገዋል

በስብሰባው ሒደት ውስጥ ለተጠየቁ የተለያዩ ጥያቄዎች ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው ተገቢና የተሰብሳቢውን ልብ ሊነካ በሚችል መልኩ መመለስ በመቻላቸው በስብሰባው ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ የተለያዩ ግለሰቦች በኢሕአፓ ስብሰባ ላይ ሲገኙ ይህ የመጀመሪያ እንደሆነና ይህ ገንቢና ትምህርታዊ ውይይት ስለ ኢሕአፓ የነበራቸውን የተሳሳተ አመለካከት ሊቀይርና ትክክለኛ አቅጣጫ ሊያሲይዝ እንደቻለ በማረጋገጥ የሕአፓን የረጅም ትግልና የአላማ ፅናትን በማድነቅ የተቃዋሚ ሀይሎች

በጋራ ሁለገብ ትግል እንድያደርጉ ኢሕአፓ ከምንግዜውም የበለጠ በዚህ የጋራ ትግል ላይ ከፍተኛ አስተዋፆ እንዲያበረክት አሳስበዋል።

ይህን ዘገባ ለማጠቃለል ያህል በስብሰባው ውስጥ ተሳታፊ ከሆኑትና የግሌን አስተያየት በማካተት እንዲህ አይነቱ ጥረት አንዳንድ ግለሰቦችን በኢሕአፓ ላይ ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ሊያስተካክል የሚችልና ብዙ ድጋፍን ሊያሰባስብ የሚችል ብሎም ሁላችንም የምንመኘውን የጋራ ትግል እውን ለማድረግ እንድንችል ሊያቀራርበንና ሊያግባባን የሚችል ጠቃሚ የሆነ ሒደት ስለሆነ ይህን መሰል በሳል የትግል ስልት ቀጣይነት እንዲኖረው ፅኑ ምኞታችንን እየገለፅን ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በዚህ ስብሰባ ላይ በመገኘት ላደረጉት ህዝባዊ ተሳትፎ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን።

ስብሰባው ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ስብሰባው ውስጥ በአካል በመገኘት ቅንና ነፃ በሆነ ስሜት የስብሰባውን ሒደት በጥሞና በመከታተል ይህን ቀስቃሽና አበረታች ዘገባ ያቀረብኩላችሁ ዘገቢ

ዓለማየሁ ሽመልስ
ከዴንቨር

# ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ